# ስለ ሥር-የሰደደ በትምህርት ገበታ ያለመገኘትን፣ የመቀነስ ጥረት (Chronic Absenteeism Reduction (CARE) ፓይለት/Pilot ፕሮጀክት፣ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች:

*በትምህርት ቤት ውስጥ የልጆችን ጤና እና በትምህርት ገበታ መገኘት (Attendance)ን ለማገዝ፤ በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች እና በዲሲ ጤና (DC Health)፣ በአካባቢው ሐኪሞች እና ነርሶች መካከል-የተደረገ ኢጋርነት*

## 1. የCARE ፕሮጀክት ምንድነው?

በዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) ውስጥ፣ ለተማሪዎቻችን ጤንነት እና ጤንነት-ጥበቃ ዋጋ እንሰጣለን። ጤናማ የሆኑ ተማሪዎች፣ ወደ ትምህርት ቤት እየተገኙ በተሻለ ሁኔታ መማር እንደሚችሉ እናውቃለን። DCPS፣ ከአካባቢው ሐኪሞች እና ነርሶች፣ እና ከዲሲ የጤና መምሪያ ጋር በመሆን፤ በትምህርት ቤት ውስጥ፣ የተማሪዎቻችንን ጤና እና በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance)ን በሚያግዝ ፕሮጀክት ላይ ኢጋርነትን መፍጠሩን ስናጋራችሁ፣ ደስታ ተሰምቶናል። ይህ ፕሮጀክት፣ በትምህርት ዓመት 2017-2018 የተጀመረ እና በትምህርት ዓመት 2022-2023ም የሚቀጥል ይሆናል።

በፓይለት ፕሮጀክቱ አማካኝነት -- ሥር-የሰደደ በትምህርት ገበታ ያለመገኘትን፣ የመቀነስ-ጥረት (**C**hronic **A**bsenteeism **R**eduction **E**ffort) ወይም **CARE** ተብሎ በሚጠራው – ደህንነቱ-በተጠበቀ ሁኔታ፣ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መረጃዎችን ከልጆቻቸው ሐኪም(ሞች)፣ ነርስ(ሶች)፣ እና የህክምና ቢሮ ሠራተኞች ጋር እንዲያጋሩ፤ ወላጆች ወይም አሳዳጊዎች፣ ለDCPS ፈቃድ ሊሰጡ ይችላሉ። ትምህርት ቤት ላለመግባት የቻሉ ልጆችን እና ቤተሰቦቻቸውን፣ ልዩ በሆነ ሁሉን-የማዳረስ (outreach) እና የህክምና እርዳታን እንዲያገኙ፣ እነዚህ የጤና እንክብካቤ-ሰጪ ባለሞያዎች፣ መስጠት እንዲችሉ ይህ መረጃ ይረዳቸዋል።

## 2. የDCPS ተማሪ፣ ወላጅ ነኝ። ይህ ፕሮጀክት ልጄን እንዴት ሊረዳው ይችላል?

ልጅዎ ትምህርት ቤት ላይገባ የሚችልበት ሁኔታ ካለ፣ ሐኪሞች፣ ነርሶች፣ እና ሠራተኞቻቸው፤ ልዩ በሆነ ሁሉን-የማዳረስ (outreach) እና የህክምና እርዳታ አገልግሎትን መስጠት ይችላሉ። ለምሳሌ፤ ልጅዎ የተሻለ ስሜት እንዲኖረው እና የልጅዎን የአስም፣ አለርጂ፣ ወይም ሌሎች ሁኔታዎችን በተሻለ ሁኔታ ለመቆጣጠር፤ የልጅዎ ሐኪም አዲስ ወይም የተለየ መድሃኒት ለመለወጥ ሃሳብ ሊያቀርብ ይችል ይሆናል። ወደ ትምህርት ቤትን በመገኘት-ላይ ተጽዕኖ ሊያደርሱ የሚችሉ - እንደ የመጓጓዣ አገልግሎት ወይም የልጅ እንክብካቤ (child care) ማስፈልግ-ያሉትን፤ ሌሎች የተለመዱ ጉዳዮች ላይ፣ የህክምና እንክብካቤ ቡድኑ እርዳታ-ሊያደርግም ይችል ይሆናል።

## 3. DCPS እና የአካባቢው ሐኪሞችና ነርሶች ይህንን ግንኙነት ለማድረግ ፍላጎት ያደረጋቸው ለምንድነው?

በትምህርት ቤት ውስጥ፣ በየቀኑ እየተገኙ፣ ለመማር ዝግጁ የሆኑ፣ በአካላዊ እና አዕምሮአዊ ጤናማ የሆኑ ልጆችን በማግኘት ላይ፣ DCPS እና የአካባቢው የህክምና አገልግሎት-ሰጪዎች፣ አብረው የሚጋሩት ግባቸው ነው። እንደ አስም (asthma)፣ አለርጂ፣ የሲክል-ሴል ደም ማነስ (sickle cell anemia)፣ እና የስኳር በሽታ ያሉ፣ ለብዙ ከህክምና ሁኔታዎች ጋር ለሚገኙ ተማሪዎች፣ አስቸጋሪ ሊሆን ይችላል። ሐኪሞች እና ነርሶች፣ ስለ ትምህርት ቤት የትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) የበለጠ ሲያውቁ፤ የተማሪዎች ጤና እና የጤንነት-ጥበቃ ላይ በተሻለ መንገድ ማገዝ መቻላችንን ለመመልከት፣ DCPSና የአካባቢ ሐኪሞች እና ነርሶች በኢጋርነት ይሰራሉ። ውሎ አድሮ፣ በመጨረሻ፤ ተማሪዎች የቀለም ትምህርታቸውን ለማሻሻል፣ ይህ ይረዳቸዋል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

## 4. በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መረጃው እንዴት ነው፣ ከትምህርት ቤቱ ወደ ልጁ ሐኪም የሚሄደው?

ከወላጆች ፈቃድ ጋር በመሆን፣ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት መረጃ (attendance information)፣ ወደ ልጁ ሐኪም በChesapeake Regional Information System for our Patients (CRISP) አማካኝነት ደህንነቱን-በጠበቀ ሁኔታ ይላካል። ይህ ክልላዊ ድርጅት፣ ዛሬ በሺዎች ለሚቆጠሩ የአካባቢው ሐኪሞች፣ ደህንነቱን-የጠበቀ የህክምና የመረጃ-ስብስብ (data)ን ማግኛ ዘዴን ያቀርባል። CRISP፣ ከበርካታ የአካባቢው ሐኪሞች የታካሚዎች ዝርዝሮች ያለው ሲሆን፣ እና የመረጃ-ስብስብ (data)ን ከልጁ ሐኪም ዝርዝሩ ውስጥ ካለው-ቢሮ ጋር ብቻ ያጋራል።

## ስለ ሥር-የሰደደ በትምህርት ገበታ ያለመገኘትን፣ የመቀነስ ጥረት (Chronic Absenteeism Reduction (CARE) ፕሮጀክት፣ ተደጋግመው የሚጠየቁ ጥያቄዎች

### 5. በፓይለት (pilot) ውስጥ ተሳታፊ የሆኑት፣ የትኞቹ ትምህርት ቤቶች ናቸው?

በአሁኑ-ጊዜ፤ የሚከተሉት ትምህርት ቤቶች፣ በ'CARE' ውስጥ ይካፈላሉ: Bancroft Elementary, Cardozo Education Campus, Columbia Heights Education Campus, H.D. Cooke Elementary, Marie Reed Elementary, Powell Elementary, Boone Elementary, Burrville Elementary, Hendley Elementary, Ketcham Elementary, Savoy Elementary, Smothers Elementary, Thomas Elementary, and Turner Elementary.

እነዚህ ትምህርት ቤቶች የተመረጡት በበርካታ ምክንያቶች ነው። በመጀመሪያ፤ ከCRISP ጋር ተካፋይ የሆኑና የህክምና አገልግሎት-ሰጪዎችን የሚያዩ በርካታ ቁጥር ያላቸው ተማሪዎች ያላቸውን እና በፓይለት (pilot) ፕሮግራሙ ለመካፈል ፍላጎት ያላቸውን ትምህርት ቤቶችን ተመልክተናል። በሁለተኛ ደረጃ፤ ከአስም እና ሌሎች የህክምና ሁኔታዎች ጋር የሚገኙ፤ እነዚህን ዓይነት ሁኔታዎች ያሏቸው ተማሪዎች በትምህርት ቤት በየቀኑ ተገኝተው ለመማር አብዛኛውን ጊዜ የበለጠ አስቸጋሪ እንደሚሆንባቸው ስለምናውቅ፤ ከዚህ ሁኔታ ጋር የሚገኙ ከፍተኛ የተማሪዎች ቁጥር ያላቸውን ትምህርት ቤቶች ፈልገናል። በመጨረሻም፤ ቤተሰቦች መሳተፍ ሲፈልጉ የስምምነት ሰነድን እና ሌላ ተጨማሪ እርምጃዎችን በመውሰድ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ፍላጎትን ያሳዩ እና ፈቃደኛ የሆኑ፤ የእንግዳ መቀበያ ቢሮ የቡድን አባላቶች የሚገኙበትን ትምህርት ቤቶች ተመልክተናል። እያንዳንዱ የፓይለት (pilot) ትምህርት ቤቶች፣ እነዚህን ምክንያቶች አሟልተዋል።

### 6. የእኔ ቤተሰብ እንዴት ሊሳተፍ ይችላል?

ለመካፈል፣ ተካፋይ በሆኑ ትምህርት ቤቶች የእንግዳ መቀበያ ዋናው ቢሮ ውስጥ፣ ከትምህርት ቤትዎ ነርስ፣ ወይም በልጅዎ የህክምና-አገልግሎት ሰጪ ቢሮ ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን፣ የ'CRISP' የስምምነት-መስጫ ቅጽን፣ እባክዎን ሞልተው ያጠናቅቁ። ቤተሰቦች ስምምነታቸውን፣ በማንኛውም ጊዜ መሰረዝ (withdraw ማድረግ) ይችላሉ።

### 7. የልጄን በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መረጃን ማግኘት የሚችሉት እነማን ናቸው?

በCRISP ውስጥ የሚካፈሉ ሐኪሞች እና ነርሶች፤ እና ልጅዎን እንደ አንደኛው ታካሚያቸው አድርገው የለዩ ብቻ፣ የልጅዎ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት የመረጃ-ስብስብ (attendance data)ን ማግኘት ይችላሉ።

### 8. በCRISP ውስጥ፤ የመረጃ-ስብስብ (data)፣ በእንዴት ያለ ሁኔታ ነው በደህንነት የተቀመጠው?

በCRISP ውስጥ የታካሚዎችን መረጃ ጠብቆ መያዝ፣ ቅድሚያ የሚሰጠው ነገር ነው። CRISP፣ የታካሚውን የጤና መረጃ ለመጠበቅ፤ ሁሉንም የስቴት እና የፌደራል የግል-ሚስጥር መጠበቅ እና የደህንነት-ጥበቃ ህጎችን ይከተላል። የ1996 የፌዴራል የጤና ኢንሹራንስ ተንቀሳቃሽነት እና ተጠያቂነት ድንጋጌ (The Federal Health Insurance Portability and Accountability Act)፤ (HIPAA) የግል ሚስጥር፣ የደህንነት-ጥበቃ እና ህግ-የመጣስ ማስታወቂያ ህጎች፤ የጤንነት መረጃዎችዎን በዋናነት የሚያስጠብቁ፣ የፌዴራል ህጎች ናቸው። CRISP፣ በእነዚህ ህጎች የተዘረዘሩትን የግል-ሚስጥርን እና የደህንነት-ጥበቃ ላይ የሚሰጠው ከለላ፤ በአነስተኛ የመለኪያ ደረጃዎች ላይ እንደሆነ ከግምት ውስጥ የሚያስገባ እና፤ አብዛኛዎቹ የCRISP ፖሊሲዎች፣ በእውን ህጉ ከሚጠይቀው፣ በላይና በእጅጉ በላቀ ሁኔታ ያከናውናል።

ደህንነቱን-በጠበቀ የመረጃ-ስብስብን (data) ማስተላለፊያ-መንገድን በመጠቀም፤ እንዳይነበቡ ተደርጎ በሚተላለፍ ኢሜል (encrypted e-mail) በሆነው፣ ወይም ደህንነቱን-በጠበቀ የድህረ-ገጽ ፖርታል (secure web-portal) እንዲገኝ የተደረገ ሆኖ፤ ሁሉም መረጃዎች ይተላለፋሉ። በተጨማሪም፣ CRISP ለሁሉም ተሳታፊ አገልግሎት ሰጪዎች፤ የማንነት-መለያ ማረጋገጫ መስፈርቶችን ማክበር እንዲችሉ፣ በCRISP እንዲገኙ የተደረጉ የመረጃ-ስብስቦች (data)ን ማግኘት የሚችሉ ሁሉም ሰዎች፣ ፈቃድ ያላቸው መሆናቸው እንዲያረጋግጡ ይጠይቃል።

### 9. በዚህ ፕሮግራም ውስጥ ከተሳተፍን፤ የልጄ የጤና መረጃዎች፣ በቀጥታ ከትምህርት ቤቱ ጋር እንዲጋራ ይደረጋል?

የለም፤ አይደረግም። በዚህ ፕሮጀክት አማካኝነት፣ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት ላይ የሚገኘው የመረጃ-ስብስብ (attendance data)፣ ወደ ህክምና ሰጪዎች የሚሄድ ይሆናል፤ ነገር ግን፣ ሌላ የተለየ የስምምነት መስጫ ሳይኖር፣ የጤና መረጃዎች ከህክምና ሰጪው ወደ ትምህርት ቤቱ አይላክም።

## 10. ወላጆች ቢያውቁት ጠቃሚ የሆኑ ሌሎች ዝርዝሮች ምንድናቸው?

በዲሲ ውስጥ፣ ሁሉም-ሊባሉ የሚችሉ የሕፃናት ሐኪሞች - በ'CRISP' ውስጥ ለመካፈል ተመዝግበዋል። ሆኖም ግን፣ ሐኪምዎ ካልሆኑ፤ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መረጃዎቹን፣ እርሱ ወይም እርሷ ሊያገኙ አይችሉም።

አንድ-ጊዜ ተማሪው ከተመዘገበ (sign up ካደረገ)፤ ተሳታፊ በሆነ በፓይለት (pilot) ትምህርት ቤቶች ውስጥ በአንደኛው ውስጥ እርሱ/እርሷ እስከተገኙ ድረስ፣ የእርሱ/እርሷ በትምህርት ገበታ መገኘትና አለመገኘት (attendance) መረጃ፣ ከእርሱ/እርሷ ሐኪም(ሞች) ወይም ነርስ(ሶች) ጋር እንዲጋራ ይደረጋል። ተማሪው ሐኪሞችን ከቀየረ፤ ሐኪሙ ያለው የታካሚዎች ዝርዝር ከተስተካከለ (updated ከሆነ) በኋላ፣ የመረጃ-ዝርዝሩ (data)፣ ከአዲሱ ሐኪም ጋር ይጋራል።

## 11. ይህን ስምምነት በየስንት ጊዜ በተደጋጋሚነት መስጠት አለብኝ?

ስምምነትዎን በፅሁፍ እንዲሰረዥ ካላደረጉ በስተቀረ፣ ይህ ስምምነት፣ ልጅዎ በDCPS ውስጥ ተመዝግቦ በቆየበት ጊዜ ውስጥ ሁሉ የሚቀጥል ይሆናል። ስምምነትዎን፣ በማንኛውም ጊዜ መሰረዝ (withdraw ማድረግ) ይችላሉ።

## 12. ስለ 'CARE ፕሮጀክት' ጥያቄዎች አሉኝ። ማንን ማነጋገር እችላለሁ?

ጥያቄዎች ካሉዋችሁ፣ ከልጅዎ ትምህርት ቤት የተማሪዎች ምዝገባ ኃላፊው (registrar)፣ የትምህርት ቤት ነርስ፣ ወይም ከህክምና ሰጪው ጋር፣ እባክዎን ይነጋገሩ። የDCPS ጤና እና የጤናማነት ቡድንን፣ በhealthservices.dcps@k12.dc.gov አማካኝነትም ማነጋገርም ትችላላችሁ።